# የሰፊው ሕዝብ ድምፅ

ለሰፊው ሕዝብ —ወዝአደር፡ገበሬ፡ነጋዴ፡ወታደር፡ምሁር— መብትና ጥቅም የሚታገል ጋዜጣ

የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ይቅደም::

ቁጥር 27 2/10/67

## ጀግናዋ ቬየትናም

ቬየትናም ነፃ አገር ሆነች::ጨካኙና አመፀኛው የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም በጦር ተንበርክኮና ተዋርዶ አገር ለቆ ወጣ::እስስተ አሜሪካ በቬየትናም ሕዝብ ላይ ይህ ነው የማይባል ጭካኔ የፈፀመችው የአለምን ጭቁን ሕዝቦች በሙሉ ቬየትናምን አይታችሁ ተቀጡ ብሎ ለማስፈራራትም ነበር::መላ የአለም ተራማጆች ደግሞ በበኩላቸው 'የቬየትናም ሕዝብ ያሸንፋል' በሚል መፈክር ስር የተሰለፉትና ዛሬም 'የቬየትናም ድል ድላችን ነው' ያሉት ይህንኑ የትግሉን አለምአቀፍ መልክ በመገንዘብ ነበር::

የቬየትናም ሕዝብ ለሰላሳ አመት ወራሪዎች የጫኑበትን ጦርነት ተቋቁሞ ዛሬ ድልን ለመጎናፀፍ የበቃው ከሰማይ የወረደ ልዩ ተሰጥዎ ስላለው አይደለም፣ ባሳየው አጅግ ታላቅ የሆነ የሃገር ፍቅርና የጀግንነት ስሜት ላይ የተደራጀና ትክክለኛ የፖለቲካ አመራር ያለው ሕዝባዊ ጦርነት ለማካሄድ በመቻሉ ነው::የቬየትናም ሕዝብ ትግል የሚያረጋግጥልን የመላው አለም ሕዝቦች አምነውባቸው ከስራ ላይ ለማዋል የሚታገሉላቸውን አንዳንድ መሰረታዊ ሃቆች ነው::እነዚህ መሰረታዊ ሃቆች ምንድናቸው?

ዛሬ ኢምፔሪያሊዝም በሰበሰ ለመውደቅ የሚንገዳገድበት ጭቁን ሕዝቦች ደግሞ ለነፃነታቸው የሚያደርጉት ትግል እያየለና ድልን እየተጎናፀፈ የሚሄድበት የታሪክ ዘመን ነው::ይህን ትግል ከግቡ ለማድረስ ኢምፔሪያሊስቶቻቸውንና ቅምጦቻቸውን ነጥሎ ለመምታት የሰፊው ሕዝብና የወገኖቹ የተደራጀ ህብረትና ተጋድሎ ያስፈልጋል::በያዝነው ዘመን ይህንን ትግል በመደባዊ አቀማመጡ በበዝባዥና በተበዝባዥ መደቦች መካከል የሰፈረው የንኡስ ከበርቴ መደብ እስከመጨረሻው ሊመራው አይችልም::የሕዝቡ ፍራቻ ስላለበት መሃል ላይ ወገቡን ይላል::ከበዝባዦች ይዋዋላል::የድሉ ዋስትና ወዝአደሩ በመደባዊ ፓርቲው ተደራጅቶ ከአርሶአደር ወገኑ ጋር አንድነቱን አጠንክሮ ሲታገልና የተቀሩትንም ፀረፊውዳልና ፀረኢምፔሪያሊስት ሃይሎች በአንድ ዲሞክራሲያዊና ሕዝባዊ ግንባር ስር ሰብስቦ ትግሉን መምራቱ ብቻ ነው::ይህ ትግል የተሰበጣጠሩ መልኮች ቢኖሩትም ኢምፔሪያሊስቶችና ቅምጦቻቸው በማያዳግም ሁኔታ የሚንበረከኩት በረጅም ጊዜ የጦር ትግል ብቻ ነው::

ይህ ሁሉ ከትልቁ የጥቅምት ሪቮሉሽን ወዲህ ከግባቸው የደረሱ አብዮቶች በሙሉ፡የቻይናም ሆነ የኮርያ፡የአልባንያም ሆነ የምስራቅ አውሮፓ አገሮች ታሪክ ደጋግሞ ያሳየው ሃቅ ነው:: የቬየትናምም ሕዝብ የረጅም ጊዜ ትግል አመፀኛውን የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም አንበርክኮ የመጨረሻውን ድል ሲጎናፀፍ ያሳየው ሃቅ ይኸው ነው:: የወዝአደር ፓርቲ፡ሕዝባዊ ግንባር፡የረጅም ጊዜ ሕዝባዊ ጦርነት ... እነዚህ ሲቀነባበሩ ሺህ ጊዜ ሃያል ቢመስል ኢምፔሪያሊዝም ይሸነፋል:: ከነዚህ አንዱ ከተዛባ ወይንም ደግሞ እስካልተሟላ ድረስ ማንም ሕዝብ ቢሆን ድልን በምንም አይነት ሊጎናፀፍ አይችልም::

ለመሆኑ የቬየትናም ሕዝብ ትግል አነሳሱ እንደምን ነበር. ይህንንስ ከላይ የጠቀስነውን ሃቅ የቬየትናም አርበኞች እንዴት ከስራ ላይ አውለው ነው አሜሪካንን ማንበርከክ የቻሉት?

ቬየትናም ከዛሬ መቶ አመታት በፊት የፈረንሳይ ቅኝ ገዥዎች ከያዟት ጀምሮ የነፃነት ተጋድሎዋን ያቋረጠችበት ወቅት የለም::ያለማቋረጥ የተካሄደው የሰላሳ አመት ጦርነት በወዝአደሩ ፓርቲ መሪነት የተጀመረው በሁለተኛው የኢምፔሪያሊስቶች ጦርነት መጀመሪያ ላይ ፈረንሳይ ድል ሆና ፋሽስት ጃፓን ቬየትናም ውስጥ እግሯን ለማስገባት ስትሞክር ነው::የቬየትናም አርበኞች አስር አመታት ያህል ቀደም ብሎ በ1923*በተቋቋመው የወዝአደር ፓርቲና ቬየትሚን በሚባለው የአርበኞች ጦር ስር ባደረጉት ተጋድሎ የተነሳ ጃፓን ስር መስደድ አልቻለችም::ይህ ትግል በመካሄድ ላይ እንዳለ ጃፓን ተሸንፋ በነሃሴ ወር 1938 እጇን ሰጠች::የአርበኞቹ መሪ ሆቺሚን

* የቀኑ አቆጣጠር እንደኢትዮጵያ አቆጣጠር ነው::

በዚሁ ወር ሃኖይ ከተማ ላይ የቬየትናምን ነፃነት አወጁ። ወር ሳይሞላው በጃፓኖች ተባርረው የነበሩት የፈረንሳይ ኢምፔሪያሊስቶች ተመልሰው 'ቀኝ ግዛታቸውን' ለመያዝ በሳይጉን በኩል ገቡ። እዚያም ባኦዳይ የተባለውን ሰው 'የቬየትናም ንጉስ' ብለው አስቀመጡት። ሳይጉንም መናገሻ ከተማ ተባለች። የነፃዩን ቬየትናምም መንግስት ለመደምሰስና የእጅ አዙር ቅኝ ግዛታቸውን ለማጠንከር ጦር አነሱ። በዚህ የተነሳ በአርበኞቹና በወራሪያቹ መካከል 9 አ፡ት የፈጀው ጦርነት ተጀመረ። በመጨረሻው በታላቁ ሆቺሚንና በጄኔራል ጂያፕ የሚመራው የቬየትሚን ጦር ሚያዝያ 29 ቀን 1946 የፈረንሳዩንና ቅምጡን መንግስት ጦር ዲየንቢየንፉ በተባለው ጦር ሜዳ በማያዳግም ሁኔታ ድል አደረጉት።

ፈረንሳይም የማትችለው ማጥ ውስጥ መግባቷን አምና በዚሁ አመት ጄኔቫ ላይ የሰላም ውል ፈርማ ሃገሯን ለቅቃ ወጣች። ይህ ውል የቬየትናምን አንድነትና ነፃነት በማያወላውል ሁኔታ አረጋገጠ። በሁለት አመትም ውስጥ ጠቅላላ ምርጫ ተደርጎ የቬየትናም ሕዝብ የሚስማማውን መንግስት እንዲያቋቁም ተወሰነ። እስከዚያው ግን ቬየትናም በሁለት ቀጠና /ዞን/ ተከፍላ የአርበኞቹ ጦር በስተሰሜን በኩል እንዲሰበሰብ ስምምነት ተደረገ።

ቀደም ብላ ለፈረንሳዮች ስንቅና መሳሪያ ስታቀብል የነበረችው አሜሪካ በቬየትናም ላይ ብቻ ሳይሆን በጠቅላላው በኢንዶቻይና መርዘኛ አይኗን ተከላ ኖሮ ይህንን ውል ሌሎች ሃያላን መንግስታት ሲፈርሙ እሷ አልፈርምም አለች። የእጅ አዙር ቅኝ ግዛት ለማቋቋምም ከስራ ላይ ለማዋል የፈረንሳዮችን ቅምጥ ንጉስ አስገልብጣ 'ሪፑብሊክ' ነው ብላ ዲየም የተባለውን ቅምጥ ፕሬዚደንት ሥልጣን ላይ ጎለተች። በነሃሴ ወር ላይ አይዘንሃወር 'የዚህ ውል አንቀጾች በአሜሪካን ላይ አይፀኑም' ብሎ ለአለም ሲገልጽ ቅምጡ ዲየም አከታትሎ ይህ ውል እንደማያስነውርና ጠቅላላ ምርጫ የተባለውንም ለማድረግ ምንም የሚያስገድደው ነገር እንደሌለ በይፋ ገለጠ።

ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የአሜሪካኖችና የቅምጦቻቸው አላማ ቬየትናምን ከፋፍለው ለመግዛት፣ የደቡቡን 'መንግስት' ማጠንከርና ሰሜን ቬየትናምን በልዩ ልዩ ሳቦታዥ አዳክሞ ሰበብ ፈልጎ መውረር እንደሆነ ገልጸ እየሆነ ሄደ። ግን የትግሉ መሪ የሆነው የቬየትናም ወዝአደሮች ፓርቲም ሆነ በጠቅላላው አርበኞችና ሰፊው ሕዝብ በእንደዚህ አይነቱ ተንኮል የሚፈታ አልነበረም። አሜሪካኖችና ቅምጦቻቸው ይህንን ኻላን ሲያወጡ የቬየትናም ሰፊ ሕዝብ ለአንድነቱ፡ለነፃነቱና ለእርምጃው ያለውን የጋለ ስሜት ከቁጥር ሳያስገቡ ነበር። ትልቁ ስህተታቸው እዚህ ላይ ነው።

በተለይ በዚህ ወቅት የቬየትናም ሕዝብ እርም ብሎ ለአሰር አመታት ያህል ባደረገው ተጋድሎ ባላገሩ ከቀላ ጉደል ነፃ ወጥቶአል፣ በነጻ ክፍለ ሃገሮች ውስጥ መሬት ለአራሹ ተከፋፍሎአል፣ የሴቶች እኩልነት መብት ተረጋግጦአል፣ ድንቁርናም በመጥፋት ላይ ነው። ገበሬው በያለበት ተደራጅቶ በየመንደሩ በመረጣቸው ወገኖቹ ራሱን ያስተዳድራል። የተለያዩ ብሄሮች በእኩልነትና በወንድማማችነት መንፈስ እጅ ለእጅ ተያይዘው እየተደጋገፉ መራመድ ጀምረዋል። ባጭሩ በሚሊዮን የሚቆጠር የቬየትናም ሰፊ ሕዝብ በነፃነትና በአንድነት ተባብሮ አዲስ ኑሮ መገንባት ጀምሮአል። በተለይም ደግሞ በሰሜን በኩል ባለው ቀጠና እንዲያውም ሶሻሊዝም ታውጆ ታላቅ አርአያነት ያለው እርምጃ መታየት ጀምሮአል።

እንግዲህ የቬየትናም ሕዝብ ሁኔታ ይህ ሲሆን አሜሪካኖችና ቅምጦቻቸው የጠነባ ስርአታቸውን በዚህ ንቁ ሕዝብ ላይ ለመጫን ከፈለጉ፣ የሕዝቡን ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለመንፈግ ከተነሱ የግድ ጭፍን በሆነ አመጽ ሕዝቡን ማስፈራራት እንዳለባቸው ተረዱ። ስለዚህም መሬታችንን መለሰን አንበጥም 'ብንሞትም ብንኖርም መሬታችን ላይ' በሚል መፈክር የተነሱትን የቀድሞ ጥበኞች 'ኮሚኒስት' እያሉ ይረሽኑ ጀመር። የቀድሞ አርበኞችን እያባደዱ ማደን፣ የጄኔቫን ውል ከስራ ላይ መዋል የሚጠይቁን አርበኛ ሁሉ፡ዲሞክራሲና ሕዝባዊ ምርጫ የሚል አገርወዳድን ሁሉ እያደኑ መፍጀት ስራቸ ብለው የያዙት ፈሊጥ ሆነ። በአሜሪካኖች መሳሪያና ዶ''ር የተነሳ በአንዳንድ ቀበሌያች የቀድሞ የጭሰኝነት ስርአት እንደገና መልሶ ማንሰራራት ጀመረ።

የቬየትናም አርበኞችና ሰፊው ሕዝብ መልሶ ጦሩን ከማንገባትና ለረጅም ጊዜ ጦርነት ከመታጠቅ ሌላ ምንም ምርጫ እንዳልተተወላቸው ተረዱ። ሰላምን፡አንድነትን፡ነፃነትን በታላቅ ጉጉት

የሚጠብቀው የቪየትናም ሕዝብ ሰላም ስለተነፈገ፡ አንድነቱ ስለፈረሰ፡ ነፃነቱ ስለተደፈረና እርም
ጃው ስለተገታ እንደገና ወደትግል እንዲገባ ተገደደ::ይህ እንግዲህ በአሜሪካን ወራሪዎች በሰላ
ማዊው የቪየትናም ሕዝብ ላይ የተጫነው ጦርነት 'ሁለተኛው የአርበኝነት ዘመን' ተብሎ የታወቀው
በ1952 የተጀመረው ተጋድሎ መሆኑ ነው::

ይህ ትግል ፍሬ ይሰጥ ዘንድ መሰብሰብና መቀነባበር እንዳለበት ስለታመነ በቪየትናም
ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ /የወዝአደሮች ፓርቲ መሆኑ ነው/ ግንባር ቀደምነት በታህሳስ ወር 1952
'የቪየትናም ነፃ አውጭ ግንባር' የተባለው ድርጅት ተቋቋመ::አሜሪካኖችም በበኩላቸው ትግሉን
በእንጭጩ ለመቅጨትና ለአካባቢውም ሆነ ለአለም ጭቁን ሕዝቦች የማያዳግም ትምህርት ለመስጠት
ተሰናዱ::ማክስዌል ቴለር የተባለው የኬኔዲ አማካሪ ለፕሬዚደንቱ 'ልዩ ጦርነት'/ስፔሻል ዋር/
የተባለውን ስልት አውጥቶ ፀደቀለት::ይህ የማክስዌል ቴለር ወገኛ ፕላን በሶስት ምእራፎች የተ
ከፈለ ሲሆን አላማው:-

1ኛ/አርበኞችን በ18 ወር ውስጥ ጨርሶ ለመደምሰስ

2ኛ/ ቅምጡን መንግስት በመሳሪያና በገንዘብ ሃይል ማጠንከርና በሌላ በኩል ደግሞ የሰ
ሜን ቪየትናምን ኢኮኖሚ በልዩ ልዩ የሳቦታዥ ድርጊቶች ማዳከምና ማዘረከረክ

3ኛ/ የቪየትናም አርበኞች ጨርሰው እንደተደመሰሱና ቅምጡ መንግስት እንደተጠናከረ፡ የሰ
ሜን ቪየትናም፡ በሳቦታዥ መዳከም እንደተረጋገጠ ሰበብ ፈልጎ መውረር የሚል ነበር::

18 ወር ይቅርና ይኸው የማክስዌል ቴለር ወገኛ ፕላን 15ኛ አመቱን አከበረ::የሆነውን
ሁሉቸንም እናውቀዋለን::አርበኞቹ እንኳን ሊደመሰሱ ይቅርና ድሉን ተጎናፀፉ::ቅምጡ መንግስት
እንኳን ሊጠናከር ይቅርና እንደእንቧይ ካብ ፈራረሰ::ሰሜን ቪየትናምም እንኳን ሊዳከም ይቅርና
ድሉን ተጎናፀፈች::አሜሪካኖች ግን አልተሳካላቸውም እንጂ ይህንን እርኩስ ፕላናቸውን ከስራ
ላይ ለማዋል ያልሞከሩት ዘዴ፡ያልተጠቀሙበት መሳሪያ፡ያልፈፀሙት ጭካኔ የለም::

ፕላኑ እንደወጣ ወዲያውኑ ቅምጡ መንግስት 500 ሺ ወታደር ተቀጠረለት::ይህ ሁሉ ሰራ
ዊት በአሜሪካን ዘመናዊ መሳሪያ ከእግር እስከራሱ ታጠቀ::'ማግ'/የጦር እርዳታ አማካሪ ቡድን/
በተባለው የአሜሪካኖች የጦር ድርጅት አማካይነት 12ሺ የአሜሪካን ወታደሮች 'አማካሪዎች' እየ
ተባሉ በጦሩ ውስጥ በያለበት ተሰኩ::/በነገራችን ላይ ይህ ስመጥፉ ማግ የተባለ የጦር ድርጅት
አሜሪካኖች የቅኝ ግዛታቸውን ለማስፋፋት በፊታውራሪነት የሚልኩት ጦር ሲሆን በኢትዮጵያም ውስጥ
አለ::/

ይህም ሆኖ ታዲያ በ18 ወር ውስጥ ይፈፀማል የተባለው 'ልዩ ጦርነት' ቢሉት ቢሉት
የሚገፋ አልሆነም::መድፍ፡መትረየስ፡ቦምብ፡የጥይት ዝናብ፡የመርዝ ጢስ፡ፀረእዝርእት ኬሚካሎች፡
ሳይንስ የፈለሰፋቸው ዘመናዊ የማጥፊያ ሃይሎች በቪየትናም ምድርና በቪየትናም ሕዝ'' ላይ ለፍ
ተሻ እየቀረቡ ይፈራረቁበት ጀመር::ግን አመት፡ሁለት አመት፡ሶስት አመት፡አራት አመት ታየ፤
አርበኞቹ አልተደመሰሱም::በቅምጠቹና በጌቶቹ መሃል መነታረክና መወነጃጀል ተፈጠረ::'ጥፋት
ከኛ አይደለም፡ከቅምጠቹ ነው' ብለው የደመደሙት ወራሪዎች ዲያም የተባለውን ቅምጥ ፕሬዚደንታቸ
ውን በህዳር ወር 1952 ዓ.ም. አስገልብጠው አሳረዱት::ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ለአራት አመታት
ያህል የቅምጦች መፈራረቅ ብቻ ሆነ::የተመቸው ስድስትም ወር እየተቀመጠ ያልቀናው ደግሞ በግ
ማሽ ቀንም እየተባረረ ወደሃያ የሚጠጉ ኩዴታዎች /መፈንቅለ መንግስቶች/ ተደረጉ::በዚህ ሁሉ
እንግዲህ ፀረሕዝብ ወገኖች የባሰውን በፖለቲካም በሞራልም እየደቀቁ ሄዱ::

አሜሪካኖች 'ልዩ ጦርነት' የሚሉት ፕላን ሲከሽፍ ተሰማቸው::ዞር ዞር የነሱው የወረራ
ጦርነት ነውና በእጅ አዙር እየተዋጉ' ነገር ከማንዛዛት' አንዴ እንደመብረቅ ቪየትናምን በቀጥታ
ወርሮ 'ነፃ መውጣት' ይሻላል የሚል ፕላን ተነደፈ::

ደግሞ ስምንት አመት ሙሉ ዋተተው 'ታክቲክ' እስኪለውጡ ድረስ ይህን ፕላን 'የተወሰነ
ጦርነት'/ሊሚትድ ዋር/ በሚል ስም አጠመቁት::ይህም ከዚያኛው የባሰ ወገኛ ፕላን ነበር::
ግን ከ360 ሺህ በላይ የአሜሪካን ወታደር ሞቶና ቆስሎ፤ በሚልዮን የሚጠጋ ሰላማዊ የቪየትናም
ሕዝብም አልቆ፤ አገሪቱዋ ተቃጥላ የቪየትናም ሕዝብ ተጥቆን እንዳልፈታ እስከተገነዘቡ ድረስ
የዚህ ፕላናቸው ፋርሽነት አልታያቸውም ነበር::ይህ 'የተወሰነ ጦርነት' ይዘቱ ምንድነው.

አሜሪካ ባላት ይህ ነው በማይባል የሰውና የጦር ሃይል አንድ ጊዜ 'እንደመብረቅ' በቪየትናም ሕዝብ ላይ ተወርዳለች::አርበኞችዋን እንዳልነበር አድርጋ ተደመሰሳለች::ሰሜን ቪየትናምን አንዱ የአሜሪካን ጄኔራል እንዳለው በልዩ ልዩ ቦምብ ዝናብ ወደ 'ድንጋይ ዘመን' መልሳ ታንበረክካለች:: እንግዲህ በዚህ መልክ አርበኞች ልጆችዋ ተደምስሰው:ምድርዋ ተቃጥሎ:የተረፈው ሕዝብዋ በማይደፈረው የአሜሪካን ክንድ ተቀጥቶ ሰጥለጥ ብሎ የተረጋጋቸውንና በአሜሪካን ወራሪዎች ብርታት 'ነፃ የወጣቸውን' ቪየትናምን መልሰው ለቅምጡ መንግስት ያስረክባሉ::'ሰላም አሜሪካ' በምድረ ቪየትናም ይወርዳል::ደቡብ ምስራቅ እስያ አርፋ ትገዛለች::የአለም ጭቁን ሕዝቦች ለማይደፈረው የአሜሪካ ክንድ ሰጥ ለጥ ብለው ይገዛሉ::ይህ 'የተወሰነ ጦርነት' የተባለው ፕላን እንዲህ እንዲህ ያሉ ቅዠቶች ነበሩበት::

ተወጥኖም አልቀረ::በዚሁ ፕላን መሰረት 'መብረቁ' የአሜሪካ ጦር በሚያዝያ ወር 1957 የመጀመሪያዎቹን 3500 ወታደሮች ይዞ ደረሰ::ትንሳ ሳይቆይ የቀደመውን ጦር ለመርዳት እየተባለ እንዲሁ አንዱ ባንዱ ላይ እየተደራረበ በ1960 ላይ የአሜሪካን ጦር ብቻውን 'አገር አስለቀቀ'፤ ብዛቱ ከግማሽ ሚሊዮን በላይ ሆነ::ወራሪውን ጦርም ለማገዝ በአካባቢው ካሉት ቅምጥና አድሃሪ መንግስታት የተውጣጣ ጦርም በቪየትናም ላይ እንዲዘምት ተደረገ::ባጭሩ በ1960 የቅምጡ መንግስትና የወራሪዎቹም ጦር ተደምሮ አንድ ሚሊዮን ሁለት መቶ ሺህ ሰው ሆነ::ለ15 ቪየትናማውያን አንድ ከአ'ር እስከራሱ የታጠቀ ወታደር ተደረገበት ማለት ነው::በዚህ ላይ የመሳሪያው ብዛቱ:አይነቱ:ረቂቅነቱ::

ነገር ግን በዚህ ሁሉ ድርጊታቸው ቀደም ሲል በእጅ አዙር ይሰሩ የነበሩት አሜሪካኖች በእርግጠኛው በወራሪ መልካቸው ተጋለጡ::በእጅ አዙሩ ጊዜ ተወናበደ ከነበረው አብዛኛው የአርበኞችን ወገን እየመረጠ ስለሄደ ወራሪዎቹና ቅምጥቻቸው በብቸኝነት ይታጠሩ ጀመር::በአለም አቀፍ ደረጃም መላው የአለም ሕዝብ /የአሜሪካን ሕዝብ ሳይቀር/ ይህንን ወረራ በጥብቅ ያወግዝ ጀመር:: የተወረረቸው ቪየትናም ጠላቷን እንድትቋቋም የሶሻሊስት አገሮች በተለይም ሕዝባዊት ቻይናና የሶቭየት ህብረት የጦር:የፖለቲካና የኢኮኖሚ እርዳታቸውን ለገሱ::በፖለቲካም ሆነ በጦር በኩል የአርበኞቹ ወገን ከመቼውም ይበልጥ ዳበረ::ይህንንም ለማረጋገጥ ወራሪዎቹ የሰውም ሆነ የመሳሪያ ሃይል እጅግ ከፍተኛ ደረጃ ደርሶአል ብለው በሚገመትበት ጊዜ በጥር ወር 1960 'ቴት ኦፌንሲቭ' የተባለውን የማጥቃት ፕላን አውጥተው የቪየትናም አርበኞች 34 ታላላቅ ከተማዎችንና ዋና ከተማዋን ሳይጉንን በተቀነባበረ ዘዴ በአንድ ጊዜ አጥቅተው ብዙዎቹን ነፃ አወጡ::ወራሪዎቹ ከተማ ከተማውን በታላቅ ጭንቅና በተለይ ደግሞ ሕዝብና ንብረትን በጭካኔ በቦምብ በመደብደብ ቢያስለቅቁም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ቅስማቸው ጨርሶ ተሰበረ ለማለት ይቻላል::

በዚሁ አመት ወራሪዎቹ መሸገው ከተቀመጡባቸው ከተማዎች በስተቀር ሃገሪቱን በሙሉ ከቁጥጥሩ ስር ያደረገው 'ብሄራዊ ነፃ አውጭ ግንባር' በፖለቲካውም በኩል ድልን በመጐናፀፍ 'ጊዜያዊ አብዮታዊ መንግስት' ተቋቋመ::በሌላ በኩል ደግሞ ጆንሰን የጦሩ ነገር እንዳላዋጣ ስለተገነዘበው ለብዙ ጊዜ አሻፈረኝ ያለውን የእርቅ ንግግር እንዲጀምር በመገደዱ በግንቦት ወር በፓሪስ ከተማ ንግግር ተጀመረ::

ነገር ግን የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ሰላም የሚፈልግ መስሎ በእርቅ ንግግሩ ውስጥ ቢሳተፍም ቅሉ የወረራ አላማውን አላለቀቀም ነበር::ስለዚህ የቪየትናምን ሕዝብ ትግል አዘንግቶ ለመደምሰስ ሰላም የሚፈልግ መስሎ አዲስ የጦር ፕላን አወጣ::ይህ ደግሞ 'ቪየትናማይዜሽን' ወይም ቪየትናማውያንን በቪየቶማውያን መውጋት የሚል ርኩስ ፕላን ነበር::

በዚህ ጦር ፕላን መሰረት አሜሪካ በምድር ለሚዋጋው የቅምጡ መንግስት ጦር መሳሪያ:የመገናኛ:የስንቅ:የአማካሪ እርዳታ እየሰጠች ወንድማማቹን ሕዝብ እርስ በርስ ለማጫረስ ወሰነች::በተጨማሪም ደግሞ ሰሜንንም ሆነ ደቡብ ቪየትናምን የአሜሪካን ፓይለቶች በአውሮፕላን ያለማቋረጥ እንዲደበድቡ አደረገች፤ የአርበኞቹን ጦር በዚህ ዘዴ ለመደምሰስና የሕዝቡንም ሞራል ለመምታት ፈለገች::በዚህ ወቅት ወራዳው ኒክሰን በተለይ ከ1960 ጀምሮ የሃገሪቱን ከተሞች:ሆስፒታሎች:ት/ቤቶች:ድልድዮች:ፋብሪካዎች: .... በጭካኔ በቦምብ በማስደብደብ እነሂትለር እንኳን ያልፈፀሙትን ወንጀል ፈጽሞአል::ለምሳሌ ያህል በ1965 በታህሳስ ወር መጨረሻ ላይ በሃኖይና በአካ

ባቢዋ በ4 ቀናት ውስጥ ወንጀለኞቹ በሰላማዊው ሕዝብና በንብረት ላይ ያዘነቡት ቦምብ ሂትለር በሁለተኛው የአለም ጦርነት በእንግሊዝ አገር ላይ ካዘነበው ቦምብ እንደሚበልጥ ይታወቃል::ይህ የወራሪዎችን ወሰን የሌለው ጭካኔ ለማሳየት ይበቃል ብለን እንገምታለን::

ግን የቪየትናም ሕዝብ ትጥቁን አልፈታም::ይህም የወራሪዎች ሶስተኛ ፕላን በመከሸፉ የተነሳ አሜሪካ ፋታ ለማግኘት በጥር ወር 1965 ወታደሮቿን ፈጽማ ከቪየትናም ምድር ለማውጣት፣ የጊዜያዊ ሪቮሉሽናዊ መንግስትን ለማወቅ፣ የቪየትናም ሕዝብ ያለአንዳች ተጽእኖ የራሱን እድል በራሱ ለመወሰን ያለውን መብት ለማወቅ የተገደደችበትን የፓሪሱን ስምምነት ፈረመች:: ከዚያም ጊዜ ወዲህ ቢሆን ይህንን ውል ለመጣስና በልዩ ልዩ ስውር ተንኮል ለማደናቀፍ በመሞከር ጦርነቱ ይኸው እስከዛሬ ድረስ አላቋረጠም ነበር::አሁን ግን ሚያዝያ 22 ቀን 1967 ዓ.ም. ለ30 አመታት ሙሉ ትጥቁን ያልፈታው ጀግናው የቪየትናም ሕዝብ አሜሪካኖች ቀምጣቸውን አግተልተለው በታላቅ ሽበርና ሽሽት ሳይጉጉን እንዲለቁ አደረጉአቸው:: የቪየትናም ሕዝብ ሙሉ በሙሉ ድልን ተቀዳጀ::

ቪየትናም ትንሽ አገር ናት::በጦርም ሆነ በኢኮኖሚ የኢምፔሪያሊስቶች ቀንደኛ ሃይል የሆነውን የአሜሪካንን ኢምፔሪያሊዝም እንደዚህ ማንበርከክ የቻለችው እንዴት ነው? የቪየትናም ሕዝብ ትግል ድልን የተጎናፀፈው ከታላቁ የጥቅምት ሪቮሉሽን ወዲህ ድልን የተጎናፀፉ አብዮቶች የተከተሉትን ሳይንሳዊ ጎዳና በመከተሉ ነው:: የቪየትናም ሕዝብ ድልን የተቀዳጀው: 1/ በሳይንሳዊ ሶሻሊዝም የታነፀ የወዝአደር ፓርቲ፣ 2/ በዚህ ፓርቲ ግንባር ቀደምነት ሌሎችም <u>የተደራጁ ፓርቲዎችና ሕዝባዊ ድርጅቶች</u> ትግላቸውን የሚያስተባብሩበት ግንባርና 3/ በዚሁ ግንባር የሚመራ የተደራጀ ሕዝባዊ ጦር ስለነበረው ነው:: የቪየትናም አርበኞች እነዚህን ሶስት ነጥቦች ከሃገራቸው ታሪክና ተጨባጭ ጊዜያዊ ሁኔታ ጋር አዛምደው ከስራ ላይ በማዋላቸው ድልን ለመቀዳጀት በቁ::

ለመሆኑ በጠቀስነው መልክ ተደራጅተው የታገሉት መደቦችና የህብረተሰብ ክፍሎች እነማን ናቸው?

በደቡብ ቪየትናም ያለውን የመደቦች አሰላለፍ ብናይ ሕዝቡ 80 ከመቶ በግብርና የሚተዳደር ሲሆን ከነዚህ ውስጥ ከግማሽ በላይ መሬት የሌላቸው ጢሰኞች ነበሩ::ከነዚህ ገበሬዎች ባለርስቶች ይህ ነው የማይባል ግፍና በደል ሲፈጽሙባቸው ኖረዋል::በአንዳንድ ቦታ ልክ እንደኛው አገር ከምርታቸው እስከቦሰተ ሩብ ድረስም ለማስረከብ የሚገደዱበት አካባቢ ይገኝ ነበር::ባጭሩ አብዛኛው የቪየትናም ሕዝብ ከባድ የፊውዳል ጭቆና የተጫነውና መሬት እንደውሃ የጠማው ሕዝብ ነበር ማለት ነው:: የቪየትናም ሪቮሉሽናውያን ይህንን ሃቅ ተረድተው ነበር::ገበሬውን ያልያዘ: ገበሬው ያላቀፈው ምንም አይነት ሪቮሉሽን ሊደረግ አለመቻሉን ስለተረዱ ከመጀመሪያው ይዘው የተነሱት መፈክር <u>መሬት ላራሹ</u> የሚለው ቢሆን አያስገርምም::

በቅኝ ገዥዎች ከመቶ አመት ወዲህ የሚስፋፋው የካፒታሊስት ስርአት ምንም እንኳን ያገሬውን ከበርቴ እንዳያድግ አፍኖ ቢይዘውም ቅሉ በህብረተሰቡ ውስጥ የወዝአደሩ መደብ ስር እንዲሰድድ አድርጉአል::ይህ መደብ በቁጥሩ እጅግ አነስተኛ ቢሆንም ከፍተኛ በዝበዛና ጭቆና ስለነበረበት የትግል መንፈሱ በጣም ከፍተኛ ነበር::ስለዚህም ከጽንሱ ጀምሮ:በተለይም የኢንዶቻይና የሰራተኞች ፓርቲ ከተቋቋመበት ከ1923 ዓ.ም. ጀምሮ ታላቅ ተጋድሎ ያደረገና በፓርቲው አማካይነት የትግሉን አመራር የጨበጠ መደብ ነው::

የነፃነት ተጋድሎ ዋና ምሰሶዎች እነዚህ መደቦች —ወዝአደሩና አርሶአደሩ— ናቸው:: የሰፊውም ሕዝብ አንድነት የተመሰረተው በወዝአደሩና በአርሶአደሩ ህብረት አካባቢ ነበር::ፊውዳሊዝምንና ኢምፔሪያሊዝምን ለመደምሰስ በተደረገው ትግል ውስጥ ሌሎችም መደቦችና የህብረተሰብ ክፍሎች ታላቅ አስተዋጽኦ አድርገዋል::እነዚህም ነጋዴዎች:ምሁራን:ዝቅተኛ የመንግስት ሰራተኞች: በተለይም ደግሞ አስተማሪዎችና ተማሪዎች ናቸው:: የቪየትናም ሰራተኞች ፓርቲ ዋና ጠላቶችን ነጥሎ ለመምታት ስለት ባለው አመራር እነዚህ ሃይሎች ሁሉ እንዲደራጁ ማገዝና ለትግሉ ማሰለፍ እንዳለበት ፈጽሞ አልሳተውም ነበር፣ ከልባቸው የትግሉ ደጋፊ እንደሆኑና በዲሞክራሲ ላይ የተመሰረተ የየራሳቸው ድርጅት እንደሚያስፈልጋቸው ያውቅ ነበር::ስለዚህም ትግሉ ሊቀነባበር የሚችለው እነዚህ ፓርቲዎችና ድርጅቶች የሚሰባሰቡበት ሕዝባዊ ግንባር ሲቋቋም መሆኑን በማመን ይህ ግን

ባር እንዲቋቋም ፓርቲው ሰትጋት ታገለ::ጋራሪያቹን ጠርሶ ለመደምሰስ የሚቻለውም በረዥም ጊዜ በሚካሄድ ሕዝባዊ ጦርነት ብቻ መሆኑን በማመን በየደረጃው የነቃና የታጠቀ ጦር አደራጀ::

የሃገሪቱን ፀረፊውዳልና ፀረኢምፔሪያሊስት ሃይሎች ለመሰብሰብ ሲል ሕዝባዊ ግንባሩ እንዲቋቋም ፓርቲው ታላቅ ተጋድሎ በማድረጉ ከላይ እንደጠቀስነው በ1952 ዓ.ም. 'የቪየትናም ነፃ አውጭ ግንባር' የተባለው ተቋቋመ::ኢምፔሪያሊስቶችና ቅምጠቻቸው የዚህን ግንባር ተወካይነት ለማጥበብና 'ኮሚኒስቶች ብቻ ናቸው' ብሎ ለማውራት ይህንን ድርጅት 'ቪየትኮንግ' ወይም የቪየትናም ኮሚኒስት የሚል ቅጽል አወጡለት::ግንባሩ የኮሚውኒስት ፓርቲው ብቻ ሳይሆን ሃገር—ወዳድና የሰፊው ሕዝብ ወገኖች ሁሉ ተደራጅተው የሚሳተፉበት ግንባር ነበር::ለዚህ ማስረጃ 'የቪየትናም ነፃ አውጭ ግንባር' ውስጥ ካሉት ድርጅቶች ዋና ዋናዎቹን መጥቀስ ብቻ ይበቃል::

ይህ ግንባር <u>ሶስት የፖለቲካ ፓርቲዎች</u> የያዘ ግንባር ነው::ከነርሱም አንደኛው:ከሁሉ ቆራጥ የሆነውና በገበሬው ትብብር የአመራሩን ቦታ የያዘው የቪየትናም ሰራተኞችና ሪቮሉሽናዊ ምሁራን 'ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ' የተባለው ነው::ከዚህ ሌላ 'ራዲካል ሶሻሊስት ፓርቲ' የተባለው አገርወዳድና ተራማጅ ምሁራን የተሰለፉበት ፓርቲ አለ::ሶስተኛ ደግሞ የሃገሩ ከበርቴዎች የተሰበሰቡበት 'ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ' የተባለው ድርጅት አለ::በተጨማሪ በግንባሩ ውስጥ የሚወከሉ የሰፊው ሕዝብ ልዩ ልዩ ድርጅቶች መአት ናቸው::ከነዚህም ውስጥ በብሄርአቀፍ ደረጃ 'የገበሬዎች ህብረት ለነፃነት':'የሰራተኞች ህብረት ለነፃነት':'የወጣቶች ፌዴሬሽን ለነፃነት':'የሴቶች ህብረት ለነፃነት':የደራስያንና የአርቲስቶች ህብረት ለነፃነት':'የቡድሃ ምእመናን የሃገር ፍቅር ማህበር':'ለእናት አገርና ለእግዚአብሄር ታማኝ ካቶሊኮች ማህበር':'አገርወዳድ ጋዜጠኞች ማህበር':'አገርወዳድ አስተማሪዎች ማህበር':'የቀድሞ አርበኞች ማህበር' ወዘተ. ይገኙበታል::

ባጭሩ ይህ ግንባር የሪቮሉሽኑ አጋዥ ሊሆኑ ይችላሉ ተብለው የሚታሰቡትን መደቦችና የህብረተሰብ ክፍሎች ጾታ:ብሄር:ሃይማኖት ... ሳይለዩ በየድርጅቶቻቸው አማካይነት የሚሳተፉበት ሰፊ ግንባር ነው::እንደዚህም ስለሆነ ይህ ግንባር በቪየትናም ምድር ላይ ከወራሪያቹና ከቅምጠቻቸው በስተቀር ሰፊውን ሕዝብ አቅፍ የያዘ ግንባር ነበር::እነዚህ ሃይሎች በግንባሩ ከፍተኛ አካላት ውስጥ ተገቢ የሆነ ተወካይነት ስላላቸው ግንባሩ የሚከተለውን የፖለቲካ መስመር ለመቀየስ ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ሙሉ በሙሉ ይሳተፋሉ::

በፖለቲካ እንደዚህ የተደራጀው የቪየትናም ሕዝብ ትግል ወራሪያቹን ለመቋቋምና ለመደምሰስ አስፈላጊ የሆነው የሕዝባዊ ጦር ድርጅት ነበረው::ሰፊው ሕዝብ በወኪሎቹ አማካይነት የሚቀይሰውን ፖለቲካ ከስራ ላይ ለማዋል እንደዚሁ በየደረጃው ሕዝቡ ራሱ የሚሳተፍበት ሙሉ የሆነ የጦር ድርጅት አለው::

የጦሩ ድርጅት ሶስት የተለያዩ በጣም የሚተጋገዙ ደረጃዎች አሉት::በመጀመሪያው ደረጃ ያሉት 'አገር ጠባቂ' የሚባለው ከየቀበሌው ገበሬዎች የተውጣጣ ሕዝባዊ ጦር ነው::በዚያው በመንደሩና ባካባቢው እርሻውን እያረሰ ጠላትን ይከላከላል::ከዚያም በሁለተኛ ደረጃ በክፍለሃገር ተወስኖ የሚሰራ ጦር አለ::በከፍተኛ ደረጃ ደግሞ ዘመናዊ ትጥቅና ትምህርት ያለው ቋሚ የሆነ ሕዝባዊ ጦርሰራዊት አለ::

ከቪየትናም ሕዝብ ትግል የሚረጋገጠው አንድ ሃቅ ይህ በፖለቲካና በጦሩ መካከል ያለው ግንኙነት ነው::እርግጥ ጦሩ የፖለቲካው ታዛዥ ነበር::ግን ደግሞ እንደከበርቴዎች አስተሳሰብ የፖለቲካው ድርጅት 'አንጐል' የጦሩ ድርጅት ደግሞ 'ክንድ' እንዳይሆኑ ጥብቅ ጥንቃቄ ይደረግ ነበር::ጦሩ እውር ዲሲፕሊን የሚከተል ጦር አልነበረም::ተዋጊዎቹ የማያቋርጥና የተጣራ የፖለቲካ ትምህርት ይሰጣቸዋል::በየክፍሉ ለዚህ ተመድበው የሚሰሩ የፖለቲካ ክበቦች አሉ::የውስጣዊ አሰራሩን ብንመለከት የጦሩ መመሪያ 'ዲሞክራቲክ ሴንትራሊዝም' የተባለው መርህ ነው::አንድ ጠላትን የማጥቃት ተግባር ከመወሰዱ በፊት ጉልቶ በሚመለከተው የጦር ቡድን ውስጥ ሰፊ የሆነ ውይይት ይደረግበታል::ስለዚህ በፖለቲካ የነቃ:በዲሞክራሲ የሚመራ ጦር በመሆኑ በሞራልም ሆነ በጀግንነት በገንዘብ ብቻ ከተገዛውና በትእዛዝ ብቻ ከሚሰራው የቅምጦች ሰራዊት ጋር ተለይ

የአሳማና የሙራል ልዩነት አለ ማለት ነው::ይህንን ልዩነት:ይህንን የሕዝቡን ጦር የበላይነት ሚልዮን አይነት መሳሪያ ቢፈስስ ሊለውጠው አይችልም::ወራሪዎቹና ቅምጦቻቸው አለገባ ያላቸው አንድ ሃቅ ይህ ነበር::

እንግዲህ የቬየትናም ሕዝብ ትግል ድልን የተጐናፀፈው ባለንበት ዘመን አንድን ሕዝባዊ ትግል ከግቡ ለማድረስ የሚያስፈልጉትን ሰስት የተያያዙ ነገሮች ከሃገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አዛምዶ ከስራ ላይ ማዋል በመቻሉ ነው::ሌላ ተአምር የለውም::

የኛም ሪቮሉሽን ፊውዳሊዝምንና ኢምፔሪያሊዝምን ደምስሶ ነፃ ኢትዮጵያ ለማቋቋም ይህንን ፍቱን የሆነ ዘዴ ከሃገራችን ታሪካዊና ጊዜያዊ ሁኔታ ጋር አዛምዶ ስራ ላይ ከማዋል ሌላ መንገድ ሊከተል አይችልም::የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ከጀግናው ቬየትናም ትግል የሚያገኛቸው ትምህርቶች በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ሊመደቡ ይችላሉ::አንደኛው አረመኔውን የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም የሚመለከት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ትግሉ እንዲቀጥል መወሰድ ያለባቸውን እርምጃ የሚመለከት ነው::

የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝምን በሚመለከተው በኩል የሚገኙትን ትምህርቶች በሰስት ዋና ሃቆች ልናጠቃልለው እንችላለን::

አንደኛ:የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ዛሬም ሆነ በመላ አለም ታሪክ ምንም አይነት ተወዳዳሪነት የሌለው ጨካኝና አረመኔ አውሬ ነው::ጅብ የማያውቁት አገር ሄዶ ቁርበት አንጥፉልኝ ይላል::ቬየትናምን ያየ ከዚህ አውሬ ጋር አይዋዘም::ሙሶሉኒ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ፡አምስት አመት ሙሉ የፈፀመውን በደል የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም በቬየትናም ሕዝብ ላይ ሃያ አመት ሙሉ እጥፍ ድርብ አድርጎ ፈጽሞታል::ፋሽስት ጣሊያን በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ እንደፈፀመቸው ሁሉ አሜሪካኖቸም ቤት እየዘጉ:ቤንዚን እያርከፈከፉ ሰላማዊ ሕዝብ በእሳት ጨርሰዋል፣ እርጉዞችን በሳንጃ እየወጉ ገድለዋል፣ አርበኞችን ከተራቡ ነብሮች ጉድጓድ ጨምረዋል፣ በአንዳንድ መንደሮች /ለምሳሌ በማይላይ/ በመንደሩ ያለውን ሰው በሙሉ አሰልፈው ለዘር እንኳን እንዳይቀር አያደረጉ ረሽነዋል፣ የአርበኞች:የሴቶች:የህፃናት አንገት እየቆረጡ ፍተግራፉን ጣልያኖች እዚህ ያደርጉ እንደነበረው 'ለመታሰቢያ እያሉ' ለወዳጆቻቸው ወደአገራቸው ልከዋል፣ አይን የሚያጠፋ:ሰውነት የሚጠብስና የሚያቃጥል ጋዝ በቬየትናም ሕዝብ ላይ አፍስሰውበታል፣ በወደቀበት አካባቢ ያለውን አየር በሙሉ በመምጠጥ ሰውን ሁሉ ትንፋሽ አሳጥቶ አፍኖ በሚገድል ቦምብ ተጠቅመዋል::በታህሳስ 1965 ዓ.ም. በአራት ቀናት ውስጥ ብቻ በሃኖይና በአካባቢዋ የተጣለው ቦምብ ፋሽስት ጀርመን በሁለተኛው አለም ጦርነት በእንግሊዝ አገር ላይ የጣለቸውን የሚስተካከል መሆኑ ተገምቶአል::በነዚህና እነዚህን በመሳሰሉት ድርጊቶች የተነሳ ከመላው አለም የተውጣጡ ሸማግሌዎች በስዊድን አገር ለዚሁ ጉዳይ ባቋቋሙት 'የበርትራንድ ራስል የፍርድ ሸንጐ' ይህ ሁሉ 'በመላ የሰው ዘር ላይ የተፈፀመ ወንጀል' ነው በማለት በተጨባጭ መረጃዎች ላይ ተመርኩዘው ፍርዳቸውን ሰጥተዋል::

ሁለተኛ:የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም የተኩላ ባህታዊ ነው::ትናንትና ሙሶሉኒ ሲገባ አወራለሁ ብሎ አይደለም፣ አገር አሰለጥናለሁ ብሎ ነበር::ዛሬ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም እኛ አገር እንደገባው ትናንትም ቬየትናም ሲገባ አሰለጥናለሁ ብሎ ነበር::በሜይ ዴይ በአል ላይ ተይዘው ከነበሩት ሰሌዳዎች አንዱ የመላ ኢትዮጵያን ሕዝብ ድምጽ የሚያስተጋባ ነው፣ 'የአሜሪካን ወዳጅነትና እርዳታ በአፍንጫችን ይውጣ' የሚል ነው::እስኪነቃበትና እስኪጋለጥ ድረስ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም የስውር ወረራውን የሚያካሂደባቸው:እኛ አገር ጨርሶ ገና ያልተጋለጡ:በቬየትናም ግን ተጋልጠው ያበቃላቸው መሰርሰሪያ ዘዴዎቹ ከአሸዋ የበዙ ናቸው::ስመጥፎው ማግ የሚሉት የጦር ድርጅት:የጦር አማካሪዎች:በየባላገሩ የሚላኩ ሚስዮናውያን:ወደሕዝቡ የሚሰረስሩ የበጐ አድራጎት ወኪሎች:'ለምርምር:ለጥናት:እንዲሁም ለማስተማር'እያሉ በየዩኒቨርሲቲውና በየመፅሀፍት ቤቱ የሚሰማሩ ሰላይ ምሁራን:የካርታ ማንሻ ድርጅቶች:በየመስሪያ ቤቱ በአማካሪነት የተቀመጡ 'አዋቂዎች' እነዚህ ሁሉ እስኪጋለጡ ድረስ ሰላማዊ መሰርሰሪያዎች:ሲጋለጡ ደግሞ እንደአበደ ውሻ የሚክለፈለፉ ተናካሽ አውሬዎች መሆናቸውን ያለፉት 20 አመታት የቬየትናም ሕዝብ ፈተና አበጥሮ ያሳየናል::

ሰስተኛው ትምህርት ደግሞ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ይሸነፋል የሚል ነው:: የኢምፔሪያሊዝምን ጠባይ ጠንቅቀው ለተረዱ የበሰበሰና ለመሞት የሚያጣጥር ካፒታሊዝም መሆኑን ለሚያውቁ ሁሉ ይህ አዲስ ነገር አይሆንባቸውም:: የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም በቪየትናም ላይ ይህንን ሁሉ በደል የፈፀመው የዚህን ሕዝብ ትግል ደምስሶ የማይደፈር ለመምሰል፣ ቪየትናምንም ለአለም ሕዝብ መቀጣጫ ለማድረግ ነበር:: የተቀጣው እርሱ ሆነ:: ይህንን ሁሉ ውርደት ተከናንቦ ሲወጣ መሰረታዊ ደካማነቱ ታየበት:: የቪየትናም ሕዝብ እንዳሸነፈው ሌሎችም የአለም ጭቁን ሕዝቦች ያሸንፉታል:: በተለይ ደግሞ በታሪኩ የወራሪዎቹን ሙከራ ደጋግሞ እያከሸፈ በመላ አለም ፊት አድናቆት ያተረፈው ጀግናው የኢትዮጵያ ሕዝብ የአሜሪካንን ኢምፔሪያሊዝም ከሃገሩ ጠራርጎ እንደሚያወጣው ፈጽሞ አንጠራጠርም:: እንዴት ለሚለው ጠያቂም የቪየትናም ሕዝብ ትግል ያረጋገጠልንን ትክክለኛ መንገድ መከተል ብቻ ነው እንላለን::

በያዝነው ክፍለ ዘመን የታዩት አብዮቶች ያረጋገጡት ሃቅ ዛሬ በአይናችን ስር በመታየት ላይ ነው:: በአሁኑ ወቅት ፊውዳሊዝምንና ኢምፔሪያሊዝምን ደምስሶ ትግሉን ከዳር ሊያደርሰው የሚችል አመራር የሰራተኛው አመራር ብቻ ነው:: በተሰበጣጠሩ ታሪካዊ ምክንያቶች በትግሉ መጀመሪያ ላይ በግንባር ቀደምነት ሊመራ የሚችለው የንኡስ ከበርቴ መደብ በበዝባዥና በተበዝባዥ መደቦች መካከል የሚፋፋመው ትግል ሲያሸብረው ይዋልላል፣ ትግሉ ከደረሰበት ቦታ ወደፊት እንዳይራመድ መፍጨርጨር ይጀምራል፣ ከያለበት ተቀስቅሶ በየአቅጣጫው እየቀደመው የሚሄደውን ትግል ለመግታት መልሶ ከአድሃሪ ሃይሎች ጋር:በተለይም ከሕዝቡ ደመኛ ጠላቶች ከኢምፔሪያሊስቶች ጋር መዋዛትና መታረቅ ይሞክራል::

ለተወሰነ ጊዜ ከሕዝቡ ጐን ተሰልፍ ይራመድ የነበረው ደርግ ዛሬ ታሪክ እየቀደመው ስለሄደ ከትግሉ ሂሳ ቶስ ቶስ በማለት ላይ ነው:: መምራት ተስኖት ለመግታት የሚፈልገውን የኢትዮጵያን ሰፊ ሕዝብ የነፃነት ትግል ወደፊት እንዳይቀጥል ፍቱን የሆኑትን የትግል ዘዴዎች አፍኖ ይዞ ይታያል::

ኢምፔሪያሊስቶችና በያለበት የሰካኩአቸው ወኪሎቻቸው የኢትዮጵያን ሕዝብ ትግል ለመቀልበስ ሴራ እየደጋገሙ በመምታት ላይ መሆናቸውን እናውቃለን:: ከእለት እለት በአድሃሪ ሃይሎች እየተመሰጠ የሚሄደው ደርግ በነዚህ ፀረሕዝቦች ላይ ጥብቅ እርምጃ በመውሰድ ፋንታ እንዲያውም የአሜሪካን ኢምፔሪያሊስቶች ስም በክፉ እንዳይነሳ ከልክሉአል:: ሕዝቡን የማስተማርና የማንቃት: ጠላቶቹን እየጠቆሙ የማሳየት ሃላፊነት ያላቸው ጋዜጦችና ሬዲዮ በዚህ በማጋለጥ ተግባር እንዳይሳተፉ ተከልክለዋል:: የዛሬ አራት አምስት ወር እንኳን ይደረግ የነበረውን ያህል ፀረኢምፔሪያሊስት ፕሮፓጋንዳ ዛሬ ማድረግ አይቻልም:: አድሃሪያቹና የኢምፔሪያሊስቶቹ ወኪሎች ቦታ ቦታ ለመያዝ ባደረጉት ትግል ጊዜያዊ ድል ስላገኙ ቡቸሎቻቸው እነበአሉ ግርማ 'የዜና አገልግሎት' የመሳሰለውን ቁልፍ ቦታ እንዲይዙ አድርገዋል::

የሰፊውን ሕዝብ ትግል በማደራጀትም በኩል ደርጉ ከንኡስ ከበርቴው መደባዊ ጥቅም ሌላ ምንም አይነት ምክንያት የማይገኝለት ፖለቲካ እኝኝ ብሎ ይዞአል:: የንኡስ ከበርቴው ጥቅም ምንድነው. የሱ ጥቅም ትግሉ አሁን ካለበት ደረጃ ባያልፍ ነው:: በአሁኑ ደረጃ ደግሞ የሰፊው ሕዝብ ጥቅም በምንም አይነት ቋሚ ዋስትና የለውም:: ይህ ከተፈለገ ሕዝቡ ራሱ ተደራጅቶ ትግሉን ከግቡ ማድረስ አለበት:: ከተደራጀ ግን ትግሉ ወደድል ያመራል ማለት ነው:: ወደድል ካመራ ደግሞ የፊውዳሊዝምና የኢምፔሪያሊዝም ጭቆና በሌላ አይነት ጭቆና አይተካም:: ንኡስ ከበርቴውም ሊዘረጋ የሚፈልገው ስርአት በትግሉ ማእበል ተጠራርጎ ይደመሰሳል ማለት ነው:: የደርጉ ንኡስ ከበርቴዎች ይህንን ፍራቻ ለመሸፈን: ትግሉ ይቀጥል የሚሏቸውን ሁሉ ደስ ሲላቸው 'አለቅጥ ተራማጅ' ይሉታል፣ ሲያሰኛቸው ደግሞ አስከናካቴው 'አድሃሪ' እያሉ ያወግዙታል::

በሌላ በኩል ደግሞ ትግሉ እንዲቀጥል የግድ አስፈላጊ የሆኑት እርምጃዎች እንዳይወሰዱ አፍነው ይዘዋል:: የሰራተኛ መደብ ፓርቲ ለትግሉ መቀጠል እንደህይወት አስተንፋስ ያስፈልገዋል:: ንኡስ ከበርቴው ወዝአደሩን እንኳን በከፍተኛ በፓርቲ ደረጃ ሲደራጅ ዝም ሊለው ይቅርና 'የሙያ ማህበርም እንኳን በዝቶብሃል' ብሎ በአዋጅ ማህበሩን ያፈርሳል:: ዛሬ የሬቮሉሽኑ ደጋፊዎች ተብለው የሚገመቱት ሃይሎች ሁሉ በየፓርቲያቸውና በየድርጅቶቻቸው አማካይነት ከትግሉ በሙሉ

ሰብ መሳተፍ ሲገባቸው እንዳይደራጁ፡ እንዳይናገሩ፡እንዳይጽፉ፡እንዳይሰበሰቡ ተከልክለው ተገሉ እጅግ የተበታተነ መልክ እንደያዘ ይገኛል::ይህም በበኩላቸው በአስደናቂ ፍጥነት በመሰብሰብና በመደራጀት ላይ ላሉት አድሃሪ ሃይሎች እጅግ አመቺ የሆነ ሁኔታ መፍጠሩን እናያለን::

ይህንን ሁሉ እየተመለከተ ደርጉ አስፈላጊዎቹን እርምጃዎች ባይወስድ መደባዊ ጥቅሙ አሸንፎት አብዮቱ እንዳይቀጥል ፍላጎት ስላደረበት ነው::ስለዚህም ዛሬ የዱላችን ፍትን ዘዴዎች ማለትም የሰራተኛው ፓርቲ እንዳይቋቋም፣ ሌሎች ፀረፊውዳልና ፀረኢምፔሪያሊስት ሃይሎች በአንድ ሕዝባዊ ግንባር ስር እንዳይተባበሩ፣ አድሃሪዎች እንዳይደመሰሱ አስፈላጊው ሕዝባዊ ጦር እንዳይቋቋም ጥረት የሚያደርጉ ሁሉ ትግሉን ለመቅጨት የሚፈልጉ፡ታሪክ አልፎአቸው የሄደ ሃይሎች ብቻ ናቸው::

ይህንንም ብንል የአንድ መደብ ታሪካዊ የአመራር ሚና ስላከተመ ብቻ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት አብሮ አከተመ ማለት አይደለም፣ ይህን የሚያደርግበት ምክንያት የለም::አብዮታውያን ይህንን ሃቅ ተገንዝበው በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በማፋፋም ላይ ያሉትን ለዲሞክራሲያዊ መብቶች የሚደረገውን ተጋድሎ በቆራጥነት መቀጠል አለባቸው::የሰራተኛው ፓርቲ መደራጀት አለበት::ሌሎቹም ተራማጅ መደቦችና የህብረተሰቡ ክፍሎች በመሰላቸው መደራጀት አለባቸው::በጠቅላላ ደግሞ የማንም አብዮት ታሪክ ደጋግሞ ያሳየን ሃቅ አለ::አድሃሪዎች በአዋጅ 'በቃችሁ' ስለተባሉ ብቻ እጅ ነስተው ከታሪክ መድረክ የወረዱበት ጊዜ የለም::ሪቮሉሽኑን /ይኸው ባገራችን እንደምናየው/ በሴራና በመሳሪያ ሃይል ለማጥፋት ይሞክራሉ::እንደዚህ ሲሆን ደግሞ ለአድሃሪዎች ፀረሕዝብ አመጽ ያለው አንዱ መፍትሄ የነቃና የተደራጀ ሕዝባዊ ጦር ብቻ ነው::ይህንን ችላ ማለት ለአድሃሪዎች ፊት መስጠትና ትግሉን ማደናቀፍ ነው::የቪየትናም ሕዝብ ድል የሚያስተምረን ይህንንም ሃቅ ጭምር ነው::

የአለም ጭቁን ሕዝቦች ትግል አይበገርም!
የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም አረመኔ ነው!
የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም የተኩላ ባህታዊ ነው!
የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ይሸነፋል!
እንደራጅ! እንደራጅ! እናሸንፋለን!!